# የየስለር ቴረስ የዜጎች
# አጥኚ ኮሚቴ
# የከተማ ልማት ዕቅድና ንድፍ መዝገበ ቃላት

በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ የሚገኙት ቃላትና ትርጉሞች ከተለያዩ የኦፊሲል ምንጮች የተሰባሰቡ ናቸው ፤ ከሲያትል ከተማ ፤ ከአሜሪካን ፕላኒንግ አሶሲዬሽን (ኤፒኤ) ፤ ከፕላነረስ ኔትዎርክ ፤ እና ከዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የንድፍና ዕቅድ ማውጫ ክፍል (2007-2008)።

## ዕቅድ ማውጣት ምንድን ነው?

የማንኛውም ዕቅድ ግብ ፤ የከተማ ፤ የአካባቢ ወይም የማህበረተሰብ ቢሆንም ፤ ለአሁንና ለወደፊት ትውልድ አመቺ ፤ ተገቢ ፤ ጤናማ ፤ ተመጣጣኝና ለዓይን የሚስቡ አካባቢዎችን በመፍጠር የሕዝብንና የማህበረተሰብን ደህንነት ማራመድ ነው።

ዕቅድ አውጪዎች ሥራቸውን በጣም ትብብር በተሞላበት ሂደት ያከናውናሉ። በዚህ የትብብር ሂደት በኩል የማህበረተሰብ ግብ እራሱን እንዲገልጽ ይረዳሉ። ከአካባቢ ነዋሪዎች ፤ ከፖለቲካ ሰዎች ፤ እና ጥቅማቸውን ከሚያስከብሩ ክፍሎች ጋር በመሥራት ዕቅድ አውጪዎች ግብን ለመምታት ይረዳሉ። ዕቅድ አውጪዎች ከብዙ ዓይነት ማህበረተሰቦች ጋር በሥራ ይተባበራሉ - ከትናንሽ መንደሮች ፤ ከትላልቅ ከተማዎች ፤ ከንዑስ የከተማ ክፍሎች ፤ ከካውንቲዎችና ከስቴቶችና ከፌደራል መሥሪያ ቤቶች ጋርም ይሠራሉ።

ይህ ግብ የሚውጣው የማህበረተሰቡ አባላት ከሚፈልጉት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ፤ በወቅቱ በሚገኙት ችግሮችና መርጃ ምንጮች መሠረት ነው። ዕቅድ አውጪዎቹ የዚህን ትንተና በማቅረብ ማህበረተሰቡ ለዕድገትና ለለውጥ ያሉትን አማራጮች እንዲመለከተ ይረዱታል።

ዕቅድ በማውጣቱ ሂደት በኩል ፤ ዕቅድ አውጪዎቹ የማህበረተሰቦችን የአካባቢ ፤ የሕብረተሰብና የኢኮኖሚ አንጻሮችን በመመልከት በመሃከላቸው ያሉትን ግንኙነቶች ያጠናሉ። በባለሙያነት የሰለጠኑት ዕቅድ አውጪዎችም በአካባቢው ውስጥ የሚገኙትን ሁኔታዎችንና የወደፊት የለውጥ አቀጣጫዎችን ያመዛዝናሉ። እንደ መጓጓዣ ፤ የመሬት አጠቃቀም ፤ መኖሪያ ቤት ፤ መዝናኛና ክፍት ቦታዎች ፤ የተፈጠርና የባህል መርጃ ምንጮች ፤ የማህበተሰብ አገልግሎቶች ፤ የሕዝብ ብዛትና የኢኮኖሚ ዕድገት የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታሉ። የራሳቸውን አሃዛዊ መረጃ (ዴታ) ከማውጣታቸውም በተጨማሪ ፤ የማህበረተሰቡን አጠቃላይ መልክ ለማዘጋጀት ዕቅድ አውጪዎች የሌሎች ክፍሎች የሥራ ውጤቶችንም ይጠቀማሉ። ዕቅድ አውጪዎች አንዴ የራሳቸውን ትንተና ካደረጉ በኋላ ፤ በተቀነባበረና አጠቃላይ በሆነ መንገድ ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ስልታዊ አማራጮችን ያወጣሉ። እነዚህ አማራጮች በወጡት ግቦችና ሥርዓት ባለው ትንተና መሠረት የወደፊት ዕድገትን ይመራሉ።

ዕቅዶች ብዙ መልኮች ሊኖራቸው ይችላል ፤ ከአጠቃላይ ዕቅዶች እስከ ታሪካዊ ቅርሶችን የማቀያ ዕቅዶችን ጨምሮ ያለውን። ዕቅዶቹን ለሚያጡ ፤ ለሚያሻሽሉና ለሥራ ለሚያፀደቁ የማህበረተሰብ ተወካዮች ፤ ነዋሪዎች ፤ የጉዳይ ተቋዳሾች ይቀርባሉ። አንዴ ዕቅዱ ከጸደቀ በኋላ ፤ የዕቅድ አውጪው ሥራ ዕቅዱን በሥራ ላይ ማዋል ፤ በብዙ ክፍሎች ውስጥ ሥራውን ማቀናበር ይሆናል። ዕቅድን ሥራ ላይ ማዋያ መንገዶች እንደ የመሬት አጠቃቀም መቆጣጠሪያዎችን ፤ የኢኮኖሚ ዕድገት ስልቶችንና የማህበረተሰብ ተሳታፊነትን የመሰሉትን ይጨምራሉ።

*ከ "ዕቅድ ማውጣት ምንድን ነው" ከሚለው የተወሰደ*
አሜሪካን ፕላኒንግ አሶሲዬሽን ፤ 2008

## የከተማ ልማት ዕቅድ ማውጫ ፡ ንድፍና የዕቅድ ማውጫ ሂደት ቃላት ፡

ከዚህ በታች የሚገኘው ማንኛውም ዕቅድ ከማውጣት ጋር ግንኙነት ባለው ስብሰባ ወይም ውይይት ወቀት ሊሰሚቸው የሚችሉት ቃላት መዝገበ ቃላት ነው። ይህ መዝገበ ቃላት የተሟላ ነው ማለት አይቻልም ፡ ይሁን እንጂ ፡ በከተማ ፡ በመኖሪያ ሠፈር ፡ በማህበረተሰብ ፡ ወይም በግለሰብ መኖሪያ ሠፈር ግንባታ ወይም ማሻሻያ ግንባታ ላይ በሚካፈሉት ዕቅድ አውጪዎች ፡ ንድፍ አውጪዎች ፡ መሐንዲሶችና አማካሪዎች ስሚነገሩ ጥቂት መሠረታዊ ቃላት የተሻለ ግንዛቤ ለማቅረብ ነው። ተገቢ በሆነበት ቦታ ሁሉ ትርጉሞቹ ለሲያትል ማህበረተሰብ ተላልፈዋል።

---

**አዲኳት ፓብሊክ ፋሲሊቲስ** ፡ ይህ ቃል እንደ መንገዶች ፡ ትምህርት ቤቶች ፡ ፍሳሽና ውሃ ለመሰሉት ብዙ ነባር የሕዝብ መገልገያዎች ለአዲሱ ግንባታ የሚሆን መጠንና ችሎታ እንዳላቸው ለመግለጽ የሚነገር ቃል ነው።

**አፎርዳብል ሃውሲንግ** ፡ በገበያ ዋጋ ያልሆነ መኖሪያ ቤት ሲሆን ፡ የተወሰኑ የገቢ ነጥቦችን ለሚያሟሉ ዜጎች ብቻ ይሰጣል። በብዙ አካባቢዎች ውስጥ ባለው የመሬትና የግንባታ ከፍተኛ ወጪ ምክንያት የመኖሪያ ቤት ወጪዎች አነስተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦች መክፈል ከሚችሉት መጠን በላይ ነው። ስለዚህ ለዚህ የሕዝብ ክፍል የመኖሪያ ቤት በገቢ አቅም እንዲሆን የሕዝብ ወይም የግል መርጃ ምንጭ ለመደጎሚያ መቅረብ አለበት።

በገቢ አቅም (አፎርዳብል) የሚለው ቃል አንጻራዊ ሲሆን በአንድ ትክክለኛ የማህበረተሰብ አማካይ የገቢ መጠን (ኤኤምአይ) ይወሰናል። ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች በጣም-የአነስተኛ-ገቢ ቤተሰቦች (ከኤኤምአይ 60 በመቶ በታች ገቢ የሚያገኙ ቤተሰቦች) ለመኖሪያ ቤት እርዳታ ብቁ መሆን የሚችሉት ክፍሎች እነሱ ብቻ ናቸው ብለው የሚያስቡ ቢሆንም ፡ በገቢ አቅም የሆነ መኖሪያ ቤት የኤኤምአይ 80 በመቶ የሆነ ገቢ ላላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች ሊሰጥ ይችላል። ዛብታም በሆኑ አካባቢዎች ውስጥ ፡ ብዙውን ጊዜ ይህ ብዙ የቢሮ ሠራተኞች ፡ አስተማሪዎች ፡ የሳት አደጋ ሠራተኞች ፡ እና የፖሊሲ ጊዶች ለዚህ ዓይነቱ መኖሪያ ቤት ብቁ እንዲሆኑ ያደርጋል ማለት ነው።

ለምሳሌ ፡ በአንድ ማህበረተሰብ ውስጥ ኤኤምአይ 100,000 ዶላር በዓመት ከሆነ እስከ 80,000 ዶላር በዓመት የሚያገኝ አንድ ቤተሰብ ብቁ ሊሆን ይችላል። በዓመት 40,000 ዶላር በሚያገኝ አንድ ቤተሰብ ፡ ከኤኤምአይ 60 በመቶ ያነሰው ፡ ማሟያ ነጥቡን በቀላሉ ያሟላል። በአንድ ማህበረተሰብ ውስጥ ያለው ኤኤምአይ 50,000 ከሆነ 40,000 የሚያገኝ ቤተሰብ ብቁ ሊሆን ይችላል።

**አምንቲ** ፡ ለነዋሪዎች የአንድን ንብረትን (ቤት) ወይም መኖሪያ ሠፈርን ተፈላጊነት ወይም አስደሳችነት ለመጨመር የሚደረጉ ዝግጅቶች ወይም ማሻሻያዎች ናቸው ፡ ለምሳሌ ፡ መናፈሻ ቦታዎች ፡ የማህበረተሰብ ማዕከላት፡ የስፖርት ሜዳዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አምንቲ የግድ አስፈላጊ አይደሉም። አምንቲ ማሳመሪያዎች ወይም አንድ ግንባታን ለገበያ ማዋያ ወይም ለሕዝብ ተጠቃሚነትን የሚጨምሩ ገጽታዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

**አርኬድ** ፡ ጣሪያ የሚደግፍ ቅስት ያለው ባንድ ወገን ክፍት የሆነ መተላለፊያ።

**አርቲኩሌሽን** ፡ የአንድ ሕንጻ ይዘት የሚገለጽበትና (መገንቢያ ቁሳቁስ ፡ ቀለም ፡ መልክ ፡ ተርታ ፡ ማስተካከያ ፡ ወዘተ) በአጠቃላይ ሕንጻው የሚገለጽበት መንገድ።

**ኦኒግ** ፡ በአንድ ቦታ ላይ ወይም ፊት ላይ የተዘረጋ ጣሪያ-መሳይ ከለላ ፡ በበረንዳ ወይም በበር ወይም በመስኮት አናት ፊት መከለያ።

**ብላይት** ፡ በከተማ ፡ በአነስተኛ ከተማ ፡ በመኖሪያ ሠፈር ክፍሎች ውስጥ ለአንድ ማህበረተሰብ የአካባቢ፡ የሕብረተሰብ ፡ እና/ወይም የኢኮኖሚ ደህንነት የሚጎዱ የንብረት አጠቃቀም ወይም ሁኔታ። "ብላይት" ያለጥቅም የተጣሉ ወይም በጣም እንክብካቤ የሚጎድላቸውን ሕንጻዎችን ፡ የተከማቸ ቆሻሻ ያለበት ክፍት ቦታ ፡ እና አደገኛ እና/ወይም ሕገ ወጥ አጠቃቀሞችን ሊያጠቃልል ይችላል።

**ብሎከ ፌስ** ፡ በአንድ መደዳ ርዝመት ከውጭ መንገድ ተይዩ የሆነ የሕንጻ የውጭ ክፍል።

**ቢልዲንግ ኮድ ፥** በመንግሥት የተዘጋጀ እንደ የሕንጻ መዋቅር ፥ የውሃና ፍሳሽ ባንቧና የኤሌክትሪክ አስፈላጊ ነጥቦችን አንድ ሕንጻ ማሟላት ያለበት የግንባታ መመሪያ።

**ቢዝነስ ዲስትሪክት ፥** የንግድ ግንባታ እንብርት ወይም የንግድ ድርጅቶች ማዕከል። የዚህ ዓይነቱ አካባቢ ድብልቅ የመሬት መጠቀሚያ ፥ የመኖሪያ ፥ የንግድና ኢንዱስትሪን ሊጨምር ይችላል።

**ካፒታል ኢምፕሩቭመንት ፕሮጀክት (ሲአይፒ) ፥** ከመሬት በላይ ወይም በታች የሚገኝ መዋቅር - ሕንጻዎችን ፥ በሕንጻ ላይ ተቀጥዮችን ፥ ድልድዮችን ፥ ቫይዳክትን (የከፍታ መንገድ) ፥ መንገዶችን ፥ የመተላለፊያ መንገዶችንና የአውራ ጎዳናዎች ማሻሻያ ግንባታን ፥ የመናፈሻ ቦታ ሥራዎችን ፥ የመስክ ቦታ ማሳመርን (ላንድሰስኬፕ) ፥ አጥር ማጠርን ፥ የውጭ በርን ፥ ምልክቶችና መብራቶችን ፥ የመንገድ ላይ መገልገያ ዕቃን ፥ እና ሌሎች ተመሳሳይ ግንባታዎችን ይጨምራሉ - እንዲሁም ማንኛውንም ከመሬት በታች የሚገነባ ዘወትር ለሕዝብ ግልጽ ሆነው የሚታዩትን ግንባታዎች - የመሬት ውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ፥ ቅስቶችንና ከመሬት ሥር መተላለፊያዎችን ያጠቃልላሉ - የከተማው ንብረት በሆነ መሬት ላይ የሚገነባ፥ በሙሉ ወይም በከፊል በከተማው ገንዘብ የሚረዳ ፥ ወይም ከከተማው ፈቃድ የሚያስፈልገው።

**ኮምፓታቢሊቲ ፥** የአንድ ሕንጻ ክፍል ከአካባቢው ከሚገኙት የሕንጻ ክፍሎች ጋር ሲነጻጸር ያለው መጠንና ሁኔታ። ለምሳሌ ፥ በአንድ ሕንጻ ፊት ላይ የሚገኙት መስኮቶች ቁመትና አመጣጠን ከእርስ በርሳቸው ጋር ፥ በመካከላቸው ካለው ክፍት ቦታ ጋርና በአካባቢው ከሚገኙት ሕንጻዎች መጠን ጋር የተዛመዱ ናቸው።

**ኮምፕሪሄንሲቭ ፕላን ፥** አጠቃላይ ዕቅድ (ኮምፕ ፕላን) ፥ ለዘላቂ የሲያትል እድገት የሚያመራ ሲሆን ፥ የሲያትልን ነዋሪዎች ቁም ጉዳዮችን ዘላቂ በሚያደርግ መንገድ የሲያትል የእድገት ግብን በትክክል እንዲገልጽ ሆኖ የተዘጋጀ የ20 ዓመት ዕቅድ ነው። "ኮምፕ ፕላን" የሲያትል ከተማ ምን ያህል እድገት እንደሚኖረውና እድገቱ በየትኛው አካባቢ መሆን እንደሚያስፈልገው ከተማው የወደፊት ውሳኔዎችን የሚመራበት የግቦችና ፖሊሲዎች ስብስብ ነው። ደግሞም በአጠቃላይ መንገድ እንዴት የእድገቱ መንስኤ በመጓጓዣና በሌላ የከተማው መገልገያዎች ላይ ሊያመጣው የሚችለውን ግፊት ይገልጻል።

የሲያትል ከተማ የስቴቱን 'ግሮዝ ማኔጅመንት አክት ኦፍ 1990" ምላሽ መጀመሪያ በ1994 ውስጥ "ኮምፕ ፕላንን" ሥራ ላይ ለማዋል ተቀበለ። የሕግ አውጭው ክፍል ውሳኔ በስቴቱ ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ካውንቲና ከተማ በስቴቱ "ኦፊስ ኦፍ ፋይናንሽያል ማኔጅመንት (ኦኤፍኤም)" የቀረበውን የታለመ እድገት ወይም "የወደፊት ሕዝብ ብዛት ግምት" ለማቀፍ የ20-ዓመት አጠቃላይ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ይጠይቃል። እነኚህ የእድገት ኢላማዎች ወደፊት ስለሚኖረው የቤተሰቦችና የሥራዎች ቁጥርን የሚያቅፍ ሲሆን በ 1992 ውስጥ ለዕቅድ ማውጫ ጉዳይ በኦኤምኤፍ የተገለጹ ሲሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለተጨማሪ 10 ዓመት ታድሷል። አጠቃላዩ ዕቅድ ለሕዝብ ደንብ የማውጫ ሂደት መሠረታዊ ሰነድ ሲሆን ፥ አንዳንዴ "ጀነራል ፕላን ወይም ማስተር ፕላን" ተብሎ ይጠራል።

**ካኖፒ ፥** የሕዝብ መተላለፊያ መንገድን ወይም የመንገድ ዳርቻ መራመጃን ከላይ መከለያ የጨርቅ ፥ የላስቲክ ፥ ወይም የተፈጥሮ ሲሆን ሊዘረጋና ሊታጠፍ የሚችል ከለላ ነው።

**ኮንቴክስት ፥** የሕንጻዎች ፥ የመንገድ መልኮችና አንድን ሕንጻ የሚያግዝ ወይም የሚያካብብ "ላንድስኬፕ" ፥ የውጭ "ሳይት" ፥ የአንድ የታወቀ ወቅት የሕንጻ አሠራር ዘዴ ወይም ቁሳቁሶች ያለው አካባቢ ፥ ሰፊ የእግር መንገድ ፥ ወይም ረጅምና ከአናት በላይ የአየር ሁኔታ መከላከያዎች ወይም በረድፍ ያሉ የመንገድ ዛፎች ሁኔታ።

**ኮንሰፕቹዋል ዲዛይን ፥** ዕቅድ የማውጫ/ንድፍ የመንደፊያ ሂደት ደረጃዎች። የጽንሰ ሃሳባዊ ንድፍ ማውጣት ደረጃ ፥ ሃሳብ ማፍለቅ ፥ ግምገማና ስለ ፕሮጀክቱ ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው። በአንድ ፕሮጀክት መጀመሪያ ላይ የሚኖር ጥሩ ጽንሰ ሃሳባዊ ንድፍ በኋላ በድጋሚ ንድፍ ለማውጣት የሚኖረውን ወጪ ያስወግዳል። ግልጽ የሆነ ጽንሰ ሃሳባዊ ንድፍ ሁሉም የፕሮጀክቱ አባላት ለታቀደው ንድፍ የጋራ ዕውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

**ክሪኤቲቭ ክላስ ፥** ዶክተር ሪቻርድ ፍሎሪዳ ፥ በቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ በሮትማን ስኩል ኦፍ ማናጅመንት የፕሮስፐሪቲ ኢንስቲቲዩት ፕሮፌሰርና ዋና ኃላፊ የሆኑት ሶሺያል ሳይንቲስት እንደሚያምኑበት እነዚህ የሕዝብ ክፍሎች በዩኤስኤ ከድህረ-ኢንዱስትሪ ለሚገኙ ከተማዎች ለኢኮኖሚ እድገት አንቀሳቃሽ ኃይል እንደሆኑ ያምናሉ። "ሃሳብ አፍላቂው" የሚለው ንጽሰ ሃሳብ አወዛጋቢ ነው ፥ የመደብ ክፍሎችን በሁለት ሰፊ ክፍሎች ይከፍላል፥ እንዲሁም ከኤስኦሲ መደባዊ የኮድ አሃዛዊ መረጃ የወጣ ነው፥

- ክሪኤቲቭ ፕሮፌሽናልስ ፡ "የእውቀት ሠራተኞችንና" ጠበቃዎችንና ሐኪሞችን እንዲያቀፍ እየሰፋ ነው።
- ሱፐር-ክሪኤቲቭ ኮር ፡ ይህ መደብ የዩኤስን ሁሉንም ሥራዎች 12 በመቶ የሚያቅፍ ሲሆን የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን (ለምሳሌ ፡ መሐንዲስ ፡ ትምህርት ፡ የኮምፒተር ፕሮግራሚንግ) ሲያቀፍ የስነ ጥበብ ፡ ንድፍ ሥራና የመገናኛ ዘደዎች ሠራተኞች ትንሹን ንዑስ ክፍል ያቀፋሉ።

ከእነዚህ ሁለት ዋነኛ ክፍሎች በተጨማሪ የ"ቦሒምያንስ" አነስተኛ ክፍልም በሃሳብ አፍላቂ መደብ ውስጥ ይጨመራሉ።

**ዲማንድ** ፡ በአንድ በተወሰነ ወቀት ላይ በተለያዩ ዋጋዎች ተጠቃሚዎች ለመግዛት ፈቃደኛ የሚሆኑበትና የግዥ አቅማቸው የሚያስችላቸው የቁሳቁሶች መጠን ነው። ገበያው ከሚያቀርበው (ሰፕላይ) ጋር ገበያተኛው የሚፈልገው (ዲማንድ) የገበያ ዋጋን ከሚወስኑት ውስጥ አንዱ ነው። እርስተን (ሪል እስቴት) በሚመለከት ረገድ "ዲማንድ" እንደ መኖሪያ ቤት በአንድ በተወሰነ ዋጋ መጠቀምን ያመለክታል <u>(ሰፕላይ የሚለውን ይመልከቱ)</u>።

**ዲሞግራፊክስ** ፡ የአንድን የሕዝብ ክፍል ቁጥር ፡ ዕድሜ ፡ ገቢና የሶሺዮኢኮኖሚ ሁኔታ የሚያመለክት የስታትስቲክስ አሃዛዊ መረጃ። እነዚህ ስታቲስቲኮች መንግሥትና የግል ንግድ ድርጅቶች ወደፊት አንድ ማህበረተሰብ ምን እንደሚመስልና የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ ለመገመት ይረዳሉ። ለምሳሌ ፡ በአንድ አካባቢ ውስጥ የሚኖሩትን ወይም ለመኖር የሚመጡትን የቤተሰቦች ቁጥር ማወቁ አዲስ ትምህርት ቤት መገንባት እንዳለበት ውሳኔ ለመስጠት ይረዳል።

**ደንስቲ** ፡ እርስተን (ሪል እስቴት) በሚመለከት ባንድ በተወሰነ መሬት ላይ ትላልቅ ወይም ረጃጅም ሕንጻዎችን መገንባት የፕሮጀክቱን ጥግግነት (ደንስቲ) ይጨምራል። ለምሳሌ ፡ የእርሶ መኖሪያ ቦታ ዙሪያ መጠን (ብሎክ) 80,000 ስኴር ጫማ ከሆነ ፡ 20,000 ስኴር ጫማ ብቻ የሚሸፍን ባለ አንድ ፎቅ ሕንጻ 80,000 ስኴር ጫማ ከሚሸፍን ባለ አንድ ፎቅ ሕንጻ ያነሰ የተጠጋጋ (ሌስ ደንስ) ነው። በተመሳሳዩም ፡ 20,000 ስኴር ጫማ የሚሸፍን ባለ አንድ ፎቅ ሕንጻ 20,000 ስኴር ጫማ ከሚሸፍን ባለ አሥር ፎቅ ሕንጻ ያነሰ የተጠጋጋ (ሌስ ደንስ) ነው።

**ደንስቲ ፐር ኤከር** ፡ የመሬት አጠቃቀም ከፍተኛነት። ለምሳሌ ፡ የ10-ኤከር የመሬት ምድብ 30 የአንድ-ቤተሰብ ቤቶችን ከያዘ የመኖሪያ ቤቱ ደንስቲ (ጥግግነት) በአንድ ኤከር 3 መኖሪያ አፓርተማዎች ነው። የነዋሪዎቹ ብዛት በአንድ ቤት ውስጥ 4 ሰው ከሆነ ፡ በአንድ ኤከር ውስጥ የሚኖረው ደንስቲ (ጥግግነት) 12 ነው።

**ዲዛይን ዲቨሎፕመንት** ፡ በመሐንዲስ የቀየሳ ሂደት ንድፍ ማውጫ ደረጃ ወቀት፡ የአሰራሩ ዘዴ ወደ ማጠቃለያው ንድፍ ይጣራል። በቀድሞቹ ደረጃዎች ላይ ፡ ትኩረት ይሰጥ የነበረው በፕሮጀክቱ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ነበር። ንድፍ በማውጣቱ ደረጃ ወቀት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ፡ ለእያንዳንዱ ቦታና ለእያንዳንዱ የፕሮጀክት ዝርዝር ሁኔታ የግል ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው።

**ዲዛይን ጋይድላየንስ** ፡ በአንድ ዓይነተኛ ከተማ ፡ ማህበረተሰብ፡ ወይም መኖሪያ ሠፈር ውስጥ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለመምራት ጥቅም ላይ የሚውሉ የንድፍ ማውጣት ወይም የማሳመሪያ መመሪያዎች። የንድፍ መመሪያዎች ባንድ ከተማ ወይም መኖሪያ ሠፈር ውስጥ የሚኖሩ አዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለማጥናት በንድፍ አጥኚ ቦርድ ሥራ ላይ ይውላሉ።

**ዲቨሎፐር** ፡ "ዲቨሎፐር" የአንድ ግንባታ ቡድን መሪ ሲሆን ፡ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ መልክ ያቀርባል። በተጨማሪም "ዲቨሎፐር" የመሬት ግዥን ፡ ንድፍ ማውጣትን ፡ የፕሮጅክት ዕቅድ ማውጣትን ፡ በገንዘብ ማገዝንና የፕሮጀክቱን ግንባታ ያስተባብራል።

**ዲስፕሌስመንት** ፡ የረጅም ጊዜ ወይም የመጀመሪያው መኖሪያ ሠፈር ነዋሪዎች በከፍተኛ የቤት ክራይ ፡ በማሻሻያ ግንባታ ፡ በጭማሪ ወለድ አገድና የንብረት ግብር ምክንያት ከአንድ ቦታ ሲዘዋወሩ።

**ኢኮኖሚክ ዲቨሎፕመንት** ፡ ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ የሚውለው የማህበረተሰብ ንብረትና የሽያጭ ግብር መሠረትን ለማስፋፋት ወይም በቢሮ ሕንጻዎች ፡ የንግድ ቤቶችና የኢንዱስትሪ ግንባታ በኩል የሚኖሩትን ሥራዎች በማስፋፋት በኩል ነው።

**ኢምፕቲ ኔስተርስ** ፡ ጎልማሳዎች ፡ ብዙውን ጊዜ ባልና ሚስት ሲሆኑ ፡ ልጆቻቸው አድገው በሌላ ቦታ የራሳቸውን የሚመሩ ናቸው ። የእነዚህ ዓይነቶች ጎልማሳዎች በባህላዊ መዝናኛዎችና በሕዝብ ተግባራት ውስጥ ተካፋይ ለመሆን ከንዑስ የከተማ

ሠፈሮች ወደ ከተማ አካባቢዎች አድራሻቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ።

**ኢንቫይሮንሜንታል ኢምፓክት ስቴትመንት (ኢአይኤስ)** ፥ በልዩ ባለሙያዎች የሚደረግ ጥናትና አንድ ፕሮጀክት መገንባቱ ከመጀመሩ በፊት በአጠቃላዩ በስቴት ወይም በፌደራል መንግሥት የሚያስፈልገው መሟላት አለበት። ፕሮጀክቱ በአካባቢና በታእታይ መዋቅር ላይ ሊኖረው ስለሚችው ግፊት ያጠናል።

**ፍሎር ኤሪያ ሬሽዮ (ኤፍኤአር)** ፥ የአንድ ሕንጻ ጠቅላላ የወለል ስፋት ሕንጻው በቀመበት አጠቃላይ የመሬት ስፋት ሲካፍል። ኤፍኤአር ብዙውን ጊዜ በዲሲማል ፍራክሽን ይገለጻል። ለምሳሌ ፥ በ 5,000 ስኴር ጫማ መሬት ላይ የቀመ የ 2,000 ስኴር ጫማ ሕንጻ 0.4 ኤፍኤአር አለው።

**ፋትፕሪንት** ፥ የአንድ ሕንጻ በውጪያዊው ስፋት መሠረተ ሕንጻው የሚይዘው የቦታ መጠን። ይህ ቁጥር ብዙውን ጊዜ በዲሲማል ይገለጻል። አንድ 50 ጫማ በ 20 ጫማ ዙሪያ ያለው ባለአንድ ፎቅ ሕንጻ የ1,000-ስኴር ጫማ ፋትፕሪንት አለው። የዚህ ዓይነት መጠን ያለው አንድ ባለ 10 ፎቅ ሕንጻ አንድ ዓይነት ፋትፕሪንት አለው ፥ ምንም እንኳ የበለጠ ከፍ ያለ ሕንጻ ቢሆንም ቀሉ።

**ጌትዌይ** ፥ ወደ አንድ ወረዳ (ዲስትሪክት) ወይም መኖሪያ ሠፈር መግቢያ ዋና ቦታ።

**ጀንትሪፊኬሽን** ፥ መኖሪያ ቤተቹ በጣም ያረጁ በመሆናቸው ምክንያት ለማሻሻያ ግንባታ ላይ የሚውል ገንዘብ መሳብ በመቻላቸውና መኖሪያዎቹ ተሻሽለው በመገንባታቸው ምክንያትና የመኖሪያዎቹ የገበያ ዋጋ የሚጨምርበት የከተማ መኖሪያ ቤት ለውጥ ሁኔታን መግለጫ ቃል ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ፥ የማሻሻያ ግንባታው ከመሆኑ በፊት ይኖሩ የነበሩት የአነስተኛ-ገቢ ነዋሪዎች ከዚያ በኋላ እዚያ ለመኖር የገቢ አቅማቸው አይፈቅድላቸውም።

**ግሪን ቢልዲንግ** ፥ ሕንጻዎች መገልገያ ምንጮችን - የኃይ ምንጭ ፥ ውሃ ፥ እና ቁሳቁሶች - በቁጠባ መጠቀም የሚችሉበትን ሁኔታ መጨመሪያ መንገድ ፥ በተሻለ አቀማመጥ ፥ ንድፍ ፥ ግንባታ ፥ አጠቃቀም ፥ ጥገናና ማስወገጃ መንገድ በኩል ሕንጻው በሰው ጤና ላይና በአካባ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት በመቀነስ።

**ግሪን ጆብስ** ፥ የ"ብሉ-ኮላር ጆብ" ሲሆን ለአካባቢ ሁኔታዎች አስቸጋሪ ነገሮች መፍትሄ ለማግኘት የተሻሻሉ ሥራዎች ናቸው። "ግሪን ጆብስ" ለአካባቢያችን ጠቃሚ ናቸው ወይም ደግሞ ቢያንስ ጎጂ አይደሉም።

**ግሮስ ፍሎር ኤሪያ (ጂኤፍኤ)** ፥ በስኴር ጫማ የሚለካ ሲሆን ፥ ከሕንጻው የውስጥ ክፍል ሲለካ የሚኖረው የአግዳሚዮሽ የወለል ስፋቶች ድምር ነው።

**ግሮዝ ማነጅመነት** ፥ በኢኮኖሚ ያደጉ ሀገሮች ካጋጠሟቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች መሃከል በይበልጥ ለኡሮ አመቺ ፥ ቀጣቢና ሥርዓት ያላቸው የከተማ አካባቢዎችን ለማዘጋጀት እንዴት የ"ግሮዝ ማነጅመነት" መመሪያዎችን ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል የሚለው ጥያቄ ነው።

በኪንግ ካውንቲ ውስጥ - ከመላው ካውንቲ የተውጣጣ የስቴቱ ግሮዝ ማነጅመነት አክት በሥራ ላይ መዋሉን የሚቆጣጠር ፥ አዲስ ቤተሰቦችና ሥራዎች እንዴትና የት መሆን እንዳለባቸው ውሳኔ የሚሰጥ ግሮዝ ማነጅመነት ፕላኒንግ ካውንስል (ጂኤምፒሲ) የሚባል የተመረጡ ሹማምንቶች ክፍል አለ። በካውንቲው ውስጥ የሚገኙት የሁሉም ከተማዎች አጠቃላይ ዕቅዶችና የካውንቲውም ዕቅዶች ከጂኤምፒሲ ውሳኔዎች መሠረተ መሆን አለባቸው።

**ኢንክሉዥናሪ ሃውሲንግ** ፥ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ የተወሰነው የመኖሪያ አፓርተማዎች ቁጥር በገቢ አቅም መሠረት መሆን እንዳለባቸው የሚያዝ።

**ኢንኩቤተር ሃውሲንግ** ፥ የአዲስ ፥ አነስተኛ-ገቢ ያላቸው የንግድ ድርጅቶች በገቢ አቅማቸው የሆነ የንግድ ቤት ወይም የኢንዱስትሪ ቦታ።

**ኢንፍራስትራክቸር** ፥ ግንባታ እንዲገነባ ለቦታው የሚቀርቡ የሕዝብ መገልገያዎች ፥ እንደ መንገዶችን ፥ ድልድዮችንና እንደ የፍሳሽና የውሃ አገልግሎት የመሰሉትን ዩቲሊቲ ጨምሮ።

**ላንድ ዩዝ** ፥

- <u>የኢንዱስትሪያዊ</u> ፣ ከምርት ፣ ማከፋፈልና ጥገና (ፒዲአር) ጋር የሚገናኙ እንደ የጅምላ ሽያጭ ፣ በፋብሪካ ማምረት ፣ በመጋዘን ማቆየት ፣ ግንባታ ፣ መገናኛ ፣ እና ዩቲሊቲ የመሰሉት።
- <u>ኦፕን ስፔስ (ክፍት ቦታ)</u> ፣ የሕዝብ ንብረት የሆኑ መናፈሻ ቦታዎች ፣ መዝናኛዎችና ክፍት ቦታዎች እንዲሁም የአውራ ጎዳና "ራይት-ኦፍ-ዌይ"።
- <u>ኦፊስ ዩዝ</u> ፣ ለአስተዳር ፣ ለመረጃና እንደ ገንዘብ ነክ ሥራዎች (ፋይናንስ) ፣ ኢንሹራንስ ፣ እና "ሪል ስቴት" ፣ ንግድ ፣ ሕግና የሕዝብ አስተዳደር ለመሰሉ የባለሙያ አገልግሎቶች።
- <u>ሚክስድ-ዩዝ</u> ፣ በአንድ ሕንጻ ውስጥ ወይም በአካባቢው ውስጥ የሚገኙ ፣ ድብልቅ መጠቀሚያዎች ፣ እንደ ጽ/ቤት ፣ ሱቅ ፣ ኢንዱስትሪና ጽ/ቤት ፣ ወይም ኢንዱስትሪና መኖሪያ ቤት ፣ ወዘተ
- <u>ሚክስድ-ሬዝደንሽያል</u> ፣ በአንድ ሕንጻ ወይም መኖሪያ ሠፈር ውስጥ የሚገኝ አንድ ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶች ያሉት መኖሪያ።
- <u>ካልቸራል/ኢንስቲቱሽናል/ኢዱኬሽናል</u> ፣ እንደ ቤተ መዘክሮች ፣ የአራዊት ማኖሪያ (ዙ) ፣ ሐኪም ቤቶች ፣ የሕክምና ማዕከሎች ፣ ኮሌጆች ፣ የስብሰባ አዳራሾች ፣ ወዘተ
- <u>ሪቴይል</u> ፣ የሱቅና ለደንበኛ የቀጥታ አገልግሎቶች ፣ መደሰቻ ቦታዎች ፣ የግል አገልግሎቶች ፣ ምግብ ቤቶችና ቡና ቤቶች ፣ የመኖሪያ ሠፈር ደንበኛን ከማስተናገድ እስከ የአካባ ደንባኛን ማስተናገድ የመሰለውን።
- <u>ቪዚተር/ሆቴል</u> ፣ ሆቴሎችና ሞቴሎች።

**ሊቭ/ወርክ ዩኒት** ፣ መኖሪያንና መሥሪያ ቦታን የሚያጣምር ቦታ።

**ሊደርሽፕ ኢን ኢነርጂ ኤንድ ኢንቫይሮንሜንታል ዲሳይን (ኤልኢኢዲ)** ፣ ለአዲስና ለነባር የንግድ ፣ የተቋምና የባለ-ብዙ ቤተሰብ መኖሪያ ሕንጻዎች የ"ግሪን ቢልዲንግ" መመዘኛ መንገድ ሲሆን "ከመላው ሕንጻ" አንፃር የአካባቢ ሁኔታ ተግባራትን ያመዛዝናል። አራት የመዘኛ ደረጃዎች አሉ ፣ ብርንዝ ፣ ስልቨር ፣ ጎልድ ፣ እና ፕላትንየም።

**ማይክሮሎን** ፣ ለአንስተኛ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች ብድር ፣ ብዙውን ጊዜ ከ1,000 ዶላር የሚያንስ ሲሆን፤ ገና ለሚጀምሩ ፣ አዲስ ለተቋቋሙ ፣ ወይም ለታዳጊ የንግድ ድርጅቶች መርጃ ነው። የፌደራል ማይክሮሎን ፕሮግራም በፌደራል መንግሥት በ1992 ውስጥ ተቋቁሞ ነበር ፤ ይሁን እንጂ፤ በመንግሥታዊ ድርጅቶችና ለትርፍ ባልቆሙ ድርጅቶች ተጨማሪ የማይክሮሎን ፕሮግራሞች የሚቀርቡም አሉ።

**ሚክስድ-ኢንካም ግሩፕስ** ፣ የአነስተኛ- ፣ የመሐከለኛ- ፣ እና የከፍተኛ-ገቢ ነዋሪዎችንና ሠራተኞችን በአንድ ሕንጻ በጥቂቱ የሚይዝ ድብልቅ።

**ሚክስድ-ዩዝ ዲቭሎፕመንት** ፣ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ የመኖሪያን ፣ የንግድን ፣ የሱቅንና ሌሎች መጠቀሚያዎችን የሚይዝ ግንባታ።

**ሞርጌጅ** ፣ ለአንድ ንብረት (ፕሮፐርቲ) የሚሰጥ ብድር ፣ ለምሳሌ መኖሪያ ቤት ወይም ጽ/ቤት ሲሆን ንብረቱ ለብድሩ ወይም ለዕዳው ክፍያ መያዣ ይሆናል።

**ናሽናል ኢንቫይሮንሜንታል ፖሊሲ አክት (ኤንኢፒኤ)** ፣ የፌደራል መሥሪያ ቤቶች ሥራ ላይ ሊያውሏቸው ላቀዷቸው እርምጃዎችና የእርምጃዎቹ ሁነኛ አማራጮች በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ግፊቶችን በማሰብ የአካባቢ ዋና ጉዳዮችን ከውሳኔዎቻቸው ጋር እንዲያጣምሩ ይጠይቃል። ይህን ነጥብ ለማሟላት ፣ የፌደራል መሥሪያ ቤቶች "ኢንቫይሮንመንታል ኢምፓክት ስቴትመንት (ኢአይኤስ) ተብሎ የሚጠራ ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጃሉ። የ"ኢንቫይሮንመንታል ፕሮተክሽን ኤጀንሲ" በሌሎች የፌደራል መሥሪያ ቤቶች የተዘጋጀውን ኤአይኤስ ተመልክቶ አስተያየት ይሰጥበታል ፤ የሁሉንም ኢአይኤስ ሀገር አቀፍ መዝገብ አያያዝ ያካሂዳል ፣ እንዲሁም የራሱም እርምጃዎች የኤንኢፒኤ መመሪያዎች ማክበራቸውን ያረጋግጣል።

**ኔበርሁድ አላያንስ** ፣ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ውስጥ የማህበረተሰብ ፍላጎትን ለማራመድ የሚቋቋም የአካባቢ ማህበረተሰብ ቡድን።

**ኔበርሁድ ማችንግ ፈንድ (ኤንኤምኤፍ)** ፣ በመኖሪያ ሠፈር አነሳሽነት ለሚከናወኑ ማሻሻያዎች ፣ ለማደራጃ ወይም እቅድ ማውጫ ፕሮጀክቶች ለሚያትል መኖሪያ ሠፈር ቡድኖችና ድርጅቶች ገንዘብ ለመስጠት በዲፓርተመንት ኦፍ ኔበርሁድ የሚተዳደር መርጃ ገንዘብ። የማህበረተሰቡ የፈቃደኝነት የጉልበት ፣ የቁሳቁስ ፣ የሙያ አገልግሎቶች ወይም የገንዘብ አስተዋጽኦ ከመዋጮው

(ከፈንዱ) በገንዘብ "እኩል መጠን" ይዋጣል።

**ኔበርሁድ ፕላን ፡** በከተማው ምክር ቤት የጸደቀ ዕቅድ ሲሆን በመኖሪያ ሠፈሮች ውስጥ ግንባታን ለመምራት ከአጠቃላዩ ዕቅድ ጋር የሚሄድ ነው ፡ እንዲሁም እንደ መኖሪያ ቤት ፡ ዋና ዋና ተቋሞችን ፡ መጓጓዣን ፡ የኢኮኖሚ እድገትንና ሌሎች የማህበረተሰብ እድገት ተግባራትን የመለሉ ግንኙነት ያላቸውን ጉዳይ ሊያካልል ይችላል።

**ኔበርሁድ ፕላኒንግ ፡** የመኖሪያ ሠፈር ዕቅድ በጂኤምኤ ለእያንዳንዱ የከተማ ክፍል የተዘጋጁት "የእድገት ኢላማዎች" ሥራ ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ላይ አስተዋጽኦ ለማድረግ ለነዋሪዎች ዕድል ይሰጣቸዋል። የእድገት ኢላማዎቹ በአጠቃላዩ ዕቅድ ላይ በ20 ዓመት ውስጥ በሲያትል ውስጥ የቤተሰቦች ቁጥር ይጨምራል ተብሎ የሚጠበቁት ነበሩ። (Hauger, 2003) ከተማው የመኖሪያ ሠፈር ዕቅድን በማውጣት ላይ አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውንም መኖሪያ ሠፈር ተጋብዞ ነበር። በምላሹም ፡ ከተማው እያንዳንዱን መኖሪያ ሠፈር ለሚረዳ አማካሪ ወጪውን የከፈለ ሲሆን ፡ ነዋሪዎቹ አማካሪዎቹን ለሥራው ቀጥረዋል።

የኔበርሁድ ፕላን (የመኖሪያ ሠፈር ዕቅድ) በማህበረተሰብ ተካፋዮች መካከል የተደረጉ በሺ የሚቆጠሩ ሰዓቶች ውይይቶችን እንዲሁም ደግሞ የብዙ የተለያዩ የጉዳዩ ተቋዳሾች ሃሳብን ያንፀባርቃል። ዕቅዱ "የከተማ የሥራ እርምጃ" በመሆን ጸድቆ ነበር። በብዙ የተለያዩ የእድገት ስልቶች ምክንያትና እንዲሁም ባንዳንድ ጉዳዮች ላይም፡ ነዋሪዎቹ ልዩ የሆነ ማህበረተሰባቸውን እንዴት አድርገው እንደሚያቀዩና እንደሚያሻሽሉ በሚገልጸው ግብ ምክንያት ፡ የማህበረተሰብ ዕቅዶቹ በአጠቃላይ ዕቅዱ ውስጥ የሚጨመር በቂ አለመዛባት አላቀረበም። በምትኩም ከተማው ከማህበረተሰብ ተወካዮች ጋር በጋራ በመሥራት ከቀሪው የአጠቃላይ ዕቅድ ቃል ጋር የሚስማማ ቃልን በመጠቀም ከመኖሪያ ሠፈር ዕቅድ ውስጥ የተወሰኑ ቃሎችን አውጥቷል - እናም ይህ ቃል በአጠቃላዩ ዕቅድ ውስጥ ገብቷል።

**ኒው ኧርባኒዝም ፡** "ኒው ኧርባኒዝም" አሜሪካዊ የከተማ ንድፍ እንቅስቃሴ ሲሆን የተጀመረው በ1980ዎቹ ውስጥ ነበር። ግቡ የተለያዩ የቤት ግንባታና የከተማ ልማት ዕቅድ ብዙ መልኮችን ለማሻሻል ነው ፡ ከተማዎችን መጠገንና የነውስ ከተማ ክፍሎች (ሰብኧርባን) ከፍት ቦታዎች ላይ መገንባትን ጨምሮ። አዲስ "ኧርባኒስት" የሆኑ መኖሪያ ሠፈሮች የተለያዩ ዓይነት መኖሪያ ቤቶችንና ሥራዎችን እንዲጨምሩና ለእግረኛ አመቺ ሁነው የተዘጋጁ ናቸው። አዲሱ "ኧርባኒዝም" (ኒዮ) የባህላዊ መኖሪያ ሠፈር ንድፍንና የሕዝብ ማጓጓዣ ላይ የሚያተኩር ግንባታን ሊጨምር ይችላል።

**ዋን ፕላኔት ሊቪንግ®፡** በባዮ ሪጅናል ዲቨሎፕመንት ግሩፕ እና በወርልድ ዋይልድላይፍ ፈንድ የተዘጋጀ ዓለም-አቀፍ ሃሳብ ሲሆን ዘላቂነት ያለው የእድገት ጽንሰ ሃሳብንና የ"ኢኮሎጂካል ፋትፕሪንቲንግ" ሃሳብን ያራምዳል። የዋን ፕላኔት ሊቪንግ® ፕሮግራም የተመሠረተው በአሥር ነጥቦች ላይ ሲሆን መመሪያዎቹ በአንድ ሁኔታ ላይ በሚኖሩት የዘላቂነት ጉዳይ አስቸጋሪ ነገሮች ላይ ለማተኮርና መፍትሄዎችን ለማዘጋጀትና ለማቅረብ መንገድ በመሆን እንደ መመሪያ ያገለግላሉ።

**ኦፕን ስፔስ ፡** የመሬት እና/ወይም የውሃ አካባቢ ሲሆን አካሉ ለሰማይ ግልጽ የሆነና ባብዛኛው ግንባታ የሌለበት ሆኖ ፡ የተካፋይነት ወይም የተመልካችነት መዝናኛ ዕድሎችን ለማቅረብ ፡ ውድ የሆኑ የተፈጥሮ ምንጮችን ለማቆየት ፡ እና የከተማ ግንባታንና ይዘትን ሥርዓት ለማውጣት ተብሎ የተከለለ ነው።

**ፔደስትሪያን ኦረንቴሽን ፡** የአንድ አካባቢ ሁኔታ ሲሆን ፡ ወደ ቦታውና ወደ ሕንጻዎች መተላለፊያው ፡ በመንገድ መሥመር ላይ የሚገኙትን መጠቀሚያዎች ፡ እንዲሁም የሱቅ መግቢያዎች የእግር መንገደኞችን ፍላጎት መሠረት የሚያደርግ ነው።

**ፕሮፖርሽን ፡** በሕንጻ ክፍሎችና ፡ "በላንድስኬፕ" እንዲሁም በአቅራቢያ በሚገኝ የግንባታ መዋቀር መካከልና በአካባቢው ማህበረተሰብ መሃከል ያለው ግንኙነት።

**ፓብሊክ ሴክተር ፡** የመንግሥት ጽ/ቤቶችና ኃላፊነቶች ነው። በኢኮኖሚ ቃል ሲገለጽ የአንድ የኢኮኖሚ ክፍል ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚመረቱበት እና/ወይም የሚሰራጩበት።

**ፓብሊክ ወርክስ ፡** የጋራ የሆነ የሕብረተሰብና የኢኮኖሚ ግቦችን ለማሟላት የውሃ ፡ የኤልክትሪክ ኃይል ፡ የቆሻሻ ማስወገጃ ፡ የመጓጓዣና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በሕዝብ መሥሪያ ቤቶች የሚንቀሳቀሱ መገልገያዎች። አንድ ታዕታይ መዋቅር

በሕዝብ አገልግሎት ክፍል በገንዘብ ካልተረዳ ፣ ካልተገነባ ፣ እና/ወይም ካልተንቀሳቀሰና ካልተጠገነ በስተቀር "ፓብሊክ ወርክስ" ተብሎ አይሰየምም።

**ሪዝም** ፣ የመስመሮች ፣ የቅርጾች ፣ ይዘቶች ፣ ወይም ቀለሞች መደበኛነትን ወይም ተስማሚነትን የሚያመለክት ሲሆን በአንድ የሕንጻ አሠራር ዘዴ ውስጥ የድግግሞሽ ጽንሰ ሃሳብን እንደ መሣሪያ በማድረግ ያዋህዳል።

**ሪድቨሎፕመንት** ፣ ባጠቃላይ አገላለጽ ፣ በከተማው ተጨባጭ ነገሮች መሠረት ለነባር ንብረቶች በድጋሚ ንድፍ ማውጣትና ማቋቋም እንዲሁም የመሬት ማሻሻያ ግንባታ።

**ሪቴይል ስፔስ** ፣ ሸቀጣ ሸቀጦች ለመሸጪያ በአንድ ሕንጻ ውስጥ የሚኖር ቦታ።

**ሪኴስት ፎር ፕሮፖዛል (አርኤፍፒ)** ፣ ከመንግሥት ወይም ከግል ድርጅት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን ገንቢዎች (ዲቨሎፐር) አንድን ንብረት ለግንባታ የሚያሻሽሉበትን መንገድ በጽሑፍ ይጠይቃል።

**ራይት ኦፍ ዌይ (አርኦደብልዩ)** ፣ አንድ ቀጭን የመሬት ቁራሽ ሲሆን በተዛዘ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለእግረኞች ፣ ለመኪናዎች ፣ ወይም ለ"ዩቲሊቲ" እንዲውል የተቀረጠ ፣ የተከበበ ፣ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል የሆነ ፣ ከአንድ ሥፍራ በላይ ወይም በታች የሚገኝ ቦታ ነው።

**ስኬርሲቲ** ፣ የሰዎች ፍላጎትና የሚያስፈልጋቸው ወሰን የሌለው በመሆኑና እነዚህን ፍላጎቶችና አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ማምረቻው ምንጭ የተወሰነ በመሆኑ ምክንያት የሚከሰት ሁኔታ ነው።

**ሾርቴጅ** ፣ በአንድ ዋጋ መጠን ተፈላጊ የሆነው (የቁሳቁስ/አገልግሎት) ብዛት ከቀረበው (ቁሳቁስ/አገልግሎት) ብዛት የበለጠ የሚሆንበት ሁኔታ።

**ስኮፕ** ፣ 1. የአንድ ተግባር ፣ ምርመራ ፣ ወዘተ ፣ ወይም ድርጊት ፣ ጽንሰ ሃሳብ ፣ ወዘተ መጠን ወይም ዘላቂነት። 2. ለአንድ ድርጊት ወይም ሃሳብ ሊኖር የሚችለው መፈናፈኛ ቦታ ወይም ዕድል።

**ሳይት አናልስስ** ፣ የአንድ የመሬት ክፍልንና አካባቢውን ለአንድ ለተወሰነ ጥቅም ተስማሚ ስለመሆኑ መወሰኛ ጥናት።

**ሳይት ኮንቴክስት** ፣ 1. ለአንድ ቦታ ወይም ፕሮጀክት ፣ ወዘተ ተገቢ የሆነ የአካባቢ ታሪክ ወይም ከባቢ።
2. ከታሪካዊና ከሕዝብ ታዕታይ መዋቅርና ከተፈጥሮና ከግንባታ አካባቢ ጋር የሚገናኝ።

**ስማርት ግሮዝ** ፣ በአጠቃላይ አነጋገር ፣ 'ስማርት ግሮዝ" በእግር መንገዶችና በብስክሌት ሊደረሱባቸው የሚችሉና የሕዝብ መጓጓዣ አገልግሎት ያላቸው ሆነው መኪና መጠቀምን የሚቀንሱ ፣ በመናፈሻ ቦታዎች ፣ በመጫወቻ ሜዳዎች ፣ እና የገበያ ሱቆች ባሉት መኖሪያ ሠፈር አካባቢ የተሰሩ የተለያዩ መኖሪያ ቤቶችን የሚያቀርቡ በይበልጥ በተከማቹ ማህበረተሰቦች ውስጥ አነስተኛ መሬት የሚወስድ ግንቦታ እንዲካሄድ የሚያበረታታ ነው።

**ስፕሮውል** ፣ የተሰራጨ ፣ በአነስተኛ የተጠጋጋ ፣ የነጠላ-ጥቅም የሆነ ፣ በመኪና አገልግሎት የተመሠረተ አጠቃቀም ሁኔታ።

**ስቴክሆልደር** ፣ በአንድ ውሳኔ ሊነኩ የሚችሉና በውሳኔው ውጤት ላይ ፍላጎት የሚኖራቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች።

**ስትሪትስኬፕ** ፣ በግንባታ መዋቅሮች ፣ መተላለፊያዎች ፣ በለምለምነቱ ፣ ክፍት ቦታ ፣ ትዕይንት ፣ ወዘተ ሁኔታዎች የሚወሰን በዓይነት የሚታይ የመንገድ ፀባይ።

**ስትዋርድሽፕ** ፣ ለአንድ ሰው ወይም ለሌሎች ለገንዘብ ነክና ለንብረት ቁጥጥርና አስተደደር።

**ስኬል ፣ ሂውማን** ፣ የግንባታ መዋቅርን ወይም የሕንጻ አሠራር ዘዴ ክፍሎችን መጠንና ተመጣጣኝነትን የሚጨምር የአንድን ሕንጻ ሁኔታ ለመግለጽ የሚውል ፣ ከሰባዊ ገጽታ ጋር የሚገናኝ እና/ወይም በውስጡ የሚገኘውን የሰባዊ ተግባርን በአሰራሩ ወይም በሕንጻው አሠራር ዘዴ ክፍሎች በኩል የሚገልጽ።

**ሴትባክ** ፡ አንድ ሕንጻ ከመንገድ ላይ ፡ ከንብረት መሥመር ላይ ፡ ወይም ከሌላ መዋቅር ላይ እንዲነሳ የሚጠይቅ ወይም የሚያደርግ።

**ሳይት ፕላን** ፡ በአንድ ቁራሽ መሬት ላይ የታቀዱ መዋቅሮችን ፡ መኪና ማቆሚያዎችን ፡ ክፍት ቦታን ፡ "ላንድስኬፕን" ፡ እና ሌሎች የግንባታ ገጽታዎችን የሚያሳይ ዝርዝር ዕቅድ።

**ሰፕላይ** ፡ በተለያዩ ዋጋዎች የሚቀርብ የቁሳቁስ ወይም የአገልግሎት ጠቅላላ መጠን ሲሆን ፡ "ሰፕላይ" ከ"ዲማንድ" ጋር በመሆን ዋጋን ከሚወስኑት ሁለት ቁልፍ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው (ዲማንድ የሚለውን ይመልከቱ)።

**ሳስቴናብል ዲዛይን** ፡ ለሕንጻዎችና "ላንድስኬፕ" ንድፍ ማውጫ ሁሉ-አቀፍ አሠራር ሲሆን ፡ የኢኮኖሚ ፡ የሕብረተሰብ ፡ እና የአካባቢ ሁኔታዎችን ሚዛን በመጠበቅ በአካባቢ ላይ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ይቀንሳል። በ2000 ውስጥ በመላው ከተማ ዘላቂነት ያለውን የሕንጻ ፖሊሲ በይፋ በማጽደቅ በሀገራችን የመጀመሪያው ከተማ ከሆነ ጀምሮ በግንባር ቀደም መሪነቱ የሲያትል ከተማ ብሔራዊ ተዋቂነትን አትርፏል። የሲያትል ዲፓርትመንት ኦፍ ፕላኒንግ ኤንድ ዲቨሎፕመንት (ዲፒዲ) በመሐንዲሶቹ ፡ በቅድ መርማሪዎቹ ፡ በኮድ አውጪዎቹ ፡ እና በዕቅድ አውጪዎቹ የዕለት ከዕለት ተግባር ውስጥ የዘላቂነት መመሪያዎችን ለማቀናበር መሥሪያ ቤቱ እየጣረ ነው።

**ተከስክ ዌስት** ፡ በቀድሞ ንብረት በመገልገል ምክንያት ሊመጣ የሚችል እንደ አስቤስቶስ ፡ ሌድ ፡ እና የዘይት ዝቃጭ የመሰሉትን የሚያጠቃልል ጎጂ ነገር። አንድ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት "ተክሲክ ዌስት" (መርዘኛ ቆሻሻ) መወገድ አለበት። ገንቢዎች (ዲቨሎፐር) አንድ ቁራሽ መሬትን ከመግዛታቸው በፊት ለመርዘኛ ቆሻሻ ምርመራ ማድረግ አለባቸው ፡ ምክንያቱም በኋላ ማጽዳቱ ጊዜ የሚወስድና ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ ሊሆን ይችላል።

**ትራንዚት ኦሮየንትድ ዲቨሎፕመንት (ቲኦዲ)** ፡ የሕዝብ ማጓጓዣ ተጠቃሚዎችንና እግረኞችን ለማበረታት የተለያዩ አገልግሎቶች (ገጽታዎች) ያሉት የሕዝብ መጓጓዣ መጠቀሚያን እንዲያስፋፋ ሆኖ የተቀየሰ የሕዝብና የንግድ አካባቢን ያሳያል። አንድ ቲኦዲ በባቡር ሐዲድ ወይም በአውቶቡስ ጣቢያ የተከበበ ማዕከላዊ ሥፍራ ያለው ሲሆን ፡ በጣም በተከማቹ መገልገያ ግንባታዎች የተከበበና የእነዚህም ግንባታዎች ከምችት ከመሃከል ራቅ በሚል ጊዜ እየቀነሰ የሚመጣ ዓይነት ነው።

**ኧርባን ፎርም** ፡ የአንድ አካባቢ ክፍፍል ሲሆን ፡ በውስጡ ባለው በተገነባው የንግባታ ብዛትና ይዘት ፡ የተፈጥሮ አካባቢና የሰዎች መዘዋወሪያ ፡ ቁሳቁሶችና መረጃ ቅንብር የሚገልጽ ነው።

**ቫኬሽን** ፡ በከተማው ምክር ቤት የሚወሰድ እርምጃ ሲሆን ፡ እንደ መንገድ ወይም መሿለኪያ መንገድ (አሌይ) ላሉት ፡ ለሕዝብ "ራይት-ኦፍ-ዌፍ" አስፈላጊነታቸው ሲያበቃ ፡ የከተማውን "ራይት-ኦፍ-ዌይ" መቀነሻን የሚያቀም ወይም የሚያጠፋ ነው።

**ቭዥን** ፡ 1. ሃሳባዊ ምስል ፤ በሃሳብ ማሰላሰል (በሃሳብ የማየት ችሎታ) 2. ሀ) የማየቻ ወይም መገነዘቢያ መንገድ (አንድ ፕሮጀክት በአንድ ሰው ግንዛቤ ዕውን ይሆናል) ለ) አርቆ የማሰብ ችሎታ ወይም ኃይል (የሀገር መሪ ታላቅ አርቆ የማየት ችሎታ)።

**ውንርፍ** ፡ የብዙት ቃሉ ውንር-ቭን ፤ ይህ የጀርመን ቃል ሲሆን ፡ ትርጉሙ ለእግረኞችና በጨዋታ ላይ ላሉ ልጆች መንገዶችን ከአደጋ የተጠበቁ ማድረጊያ ቃል ነው። ብዙውን ጊዜም በእንግሊዘኛ "ሊቪንግ ስትሪት" ፡ "ሊቪንግ ያርድ" ፡ ወይም "ሆም ዞን" ተብሎ ይተረጎማል ፤ ውንርፍ በእግረኞችና በመኪናዎች በጋራ ጥቅም ላይ የሚውል አካባቢ ነው። የመንገድ ምልክቶች ፡ የትራፊክ ምልክቶች ፡ የመንገድ መሥመሮች ፡ ወይም የመንገድ ዳርቻ ስለሌሉ ከአደጋ መጠበቁ የዚያ ውጤት ነው ፤ ይህም መኪናዎች በጣም ቀስ ብለው ስለሚሄዱ ጥቂት አደጋዎች ይኖራሉ።

**ኧርባን ቪሌጅ** ፡ በ20 ዓመት ላይ የአጠቃላይ ዕቅዱ የበለጠው የእድገት መጠንና ለውጥ ሊታይ የሚችልበት እንደ የተሻሻሉ መንገዶችና የመንገድ ዳርቻ የእግር መንገዶች ፡ ክፍት ቦታ ፡ ወዘተ የመሳሰሉት መገልገያዎች ወደፊት የሚኖረውን እድገት ለማስተናገድ ተገንብተዋል።

**ዞኒንግ ማፕ** ፡ በእያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር ውስጥ የአገልግሎት ምድብን የሚያሳይ ካርታ (ደግሞም ዞኒንግ ኦርዲናንስ የሚለውን ይመልከቱ)።

**ዞኒንግ ኦርዲናንስ ፡** ለእያንዳንዱ የመሬት ምደባ አጠቃቀም አስፈላጊ ነጥቦችን የሚገልጽ ሰነድ። እያንዳንዱ አጠቃቀም የወለል ስፋት ማወዳደሪያ (ሬሾ) ፡ የሕንጻ ቁመትና ጉዳቱ ፡ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ፡ "ላንድስኬፕ" እና/ወይም ክፍት ቦታን የሚመለከት ምድብ አስፈላጊ ነጥቦች አሉት። (ደግሞም ዞኒንግ ማፕ የሚለውን ይመልከቱ)።